# <u>ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል</u>
# <u>38 ኛ ሳምንት</u>
# <u>የቅዱስ ጴጥሮስ ሰማዕትነት</u>

<u>*ዓላማ*</u>

- ስለሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ሕይወትና ሰማዕትነት መማር

<u>የሚጠና ጥቅስ</u>

- ***"እውነት እውነት እልሃሁ፣ አንተ ጉልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደምትወደው ትሄድ ነበር ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ ሌላውም ያስታጥቅሃል ወደ ማትወደውም ይወስድሃል።***ዮሐ. 21፣18

<u>ምንባባት</u>

- ወንጌል፣ የቅዱ ጵጥሮስ መልእክታት እና ስንክሳር።

<u>*መግቢያ*</u>

- ሰማዕትነት ምን እንደሆነ ታስታውሳላችሁ? ዛሬ ከ12 ደቀመዛርቱ አንዱ ስለሆነው ስለ ቅዱስ ጵጥሮስ ሰማዕትነት እንማራለን።

- በትምህርቱም ደቀመዝሙር ከመሆኑ በፊት ምን ይሠራ እንደነበርና ስለ ሐዋርያነቱም እንማራለን።

<u>ትምህርቱ</u>

- ቅዱስ ጴጥሮስ የጌታችን ደቀመዝሙር ከመሆኑ በፊት ዓሣ አጥማጅ ነበር።ጌታችን እርሱንና ወንድሙን እንድርያስን ደቀመዛሙርቱ እንዲሆኑ ጠራቸው።

- አንድ ቀን መድኃኒታችን ደቀመዛሙርቱን ሰብስቦ ***"ሰዎች ማን ይሉኛል? "***አላቸው። እነርሱም መልሰው ***"አንዳንዶች መጥምቁ ዮሐንስ ፣ ሌሎች ኤልያስ አንዳንዶች ደግሞ ኤርምያስ ወይም ከነቢያቱ አንዱ ነህ ይላሉ።"*** አሉት።

- ጌታችንም እናንተስ ማን እንደሆንኩ ትላላችሁ? ሲላቸው ጴጥሮስ መልሦ ***"አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ"*** አለው።በእምነቱ ምክንያቱም ጌታችን እንዲህ አለው፡-***አንተ ዓለት ነህ /ጴጥሮስ ዓለት ማለት ነው።/በዚህችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ።***

- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተያዘበት ሌሊት ምን እንደሚያደርጉት ለማየት ቅዱስ ጴጥሮስ ሄዶ ነበር።ነገር ግን ከእርሱ ጋር ነበርክ ሲሉት አላውቀውም ብሎ ሦስቴ ካደ በኖላም ንስሀ ገብቶ መሪር እንባ አለቀሰ።

- ከክርስቶስ ትንሳኤ በኖላም ***"ግልገሎቼን አሰማራ... ጠቦቶቼን ጠብቅ... በጎቼን አሰማራ።"*** ብሎ ምዕመናንን ለቅዱስ ጴጥሮስ አደራ ሰጥቶታል።

- በበዓለ ሐምሳ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ቅዱስ ጵጥሮስ ሙሉ ሕይወቱን ምዕመናን ወንጌል በማስተማር አሳልፎዋል።

- በበዓለ ጰራቅሊጦስ ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ክርስቶስ ሲመሠክር 3000 /ሦስት መቶ/ ሰዎች አምነው ተጠምቀዋል። ብዙ ተዓምራትንም ይፈጽም ነበር። በጥላው ብቻ ከህመማቸው የዳኑ አሉ።

- በኋላም ለማስተማር ወደ ሮም ሄደ። የሮሙ ንጉስ ኔሮን አስሮ በመስቀል ላይ ተሠቅሎ እንዲሞት ፈረደበት።

- ቅዱስ ጴጥሮስም ስለ ክርስቶስ መሞት እንደሚፈልግ ነግሮቸው።ከጌታው ጋር እኩል እንዳይሆን ዘቅዝቀው እንዲሰቅሉት ጠየቃቸው።የሰማዕትነት አክሊል ሐምሌ 5 ቀን ተቀበለ።ቅዱስ ጴጥሮስ ሁለት መልእክት ጽፎአል።

<u>*ከታሪኩ የምንወስዳቸው ጠቃሚ መልእክቶች*</u>

- ቅዱስ ጴጥሮስ ለመኖር ዓሣ ያጠምድ ነበር።በጌታችን ከተጠራ በኋላ ግን ሕይወቱን በሙሉ ሰዎችን ለክርስቶስ በመማረክ ኖረ። ከእኛም እግዚአብሔር ጥቂት ሰማዕትነት ይጠብቃል።ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት፣ በጾጥታ መቀመጥ፣ ማስቀደስ ለእግዚአብሔር የምንከፍላቸው ጥቂት መስዋዕትነቶች ናቸው።

- ቅዱስ ጴትሮስ አለውቀውም ብሎ ክዶ ንሰሐ እንደገባ። ስናጠፋ ንሰሐ መግባት አለብን፣ ስለኃጢአታችን ንስሐ ስንገባ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ሁሌም ዝግጁ ነው። ይሄንንም ቅዱስ ጴጥሮስ ንስሐ ከገባ በምዕመናን ላይ በመሾሙ እንረዳለን።

- ቅዱስ ጴጥሮስ መልእክቱን የጻፈው ለእኛ ነውና ለመንፈሳዊው፤የጽድቅ ሕይወት ልንጠቀምባቸው ይገባል። ከሕይወቱ እንደምንማር ከመልእክቱም መማር አለብን።

<u>*ማጠቀለያ*</u>

- ቅዱስ ጴጥሮስ ከ 12ቱ ሐዋርያት አንዱ ነው።ቤተክርስቲያኔን በአንተ አለትነት እስራታለሁ ስላለውም የሐዋርያት አለቃ /ሊቀ ሐዋርያ/ ነው።

- በድሎ ንሰሐ ከገባ በኋላ የእግዚአብሔርን መንጋ የመጠበቅ ኃላፊነት የተሠጠው ለቅ. ጴጥሮስ ነው።ሕይወቱንም በመሰበክ፣ ቤተክርስቲያንንም በመጠበቅ አሳልፎ ሐምሌ 5 በሰማዕትነት አርፏል።

<u>*ጥያቄና መልመጃዎች*</u>

1. ቅዱ ጴጥሮስ ደቀመዝሙር ከመሆኑ በፊት ምን ይሠራ ነበር።
2. ጌታችን ማን ትሉኛላችሁ? ሲል ጴጥሮስ ምን ብሎ መለሰ?
3. ቅዱስ ጴጥሮስ ሊቀሐዋርያት የሚባለው ለምንድነው?
4. ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታን መቼ ከዳው በኋላስ ምን አደረገ?
5. ክርስቶስ ለቅዱስ ጴጥሮስ የሠጠው ኃላፊነት ምንድነው?
6. ከቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት በኋላ በበዓለ ጰንጠቆስጤ ስንት ሰዎች አመኑና ተጠመቁ? ቅዱስ ጴጥሮስ የት ሰማዕትነት ተቀበለ? እንዴት?

**ይቆየን።**